# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 257 ሚያዚያ 17 2005 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

**ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ዛሬም ቢሆን የህዝባችን ሰበአዊ መብትና ነጻነትን ገፈው ሕግን ያፈረሱ ህገ አራዊት የሆኑትን ወያኔዎች ከሀገራችን ምድር ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ በማስወገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በእኩልነትና በነጻነት የሚኖርባትን ሀገር ለመመስረት የሚያደርገውን የትግል ጉዞ ይቀጥላል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## በአፋር ክልል የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች የሚኖሩበትን ቦታ እኛዉ እናስተዳድዉ የሚል ጥያቄ ማቅረባቸዉ ተሰማ

የአማራን ተወላጆች የገቡበት ቦታ ሁሉ እየገባ ወደ ክልላችሁ ሂዱ እያለና ንብረታቸዉን እየቀማ የሚያፈናቅለዉ የወያኔ አገዛዝ ታማኝ የሆኑ የትግራይ ተወላጆች አፋር ክልል ዉስጥ በብዛት ሰፍረዉ በሚገኙበት ቦታ እራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር መብት የስጠን የሚል ጥያቄ ማቅረባቸዉን ከሰሞኑ ከወደ አፋር ክልል የነፈሰዉ ዜና አስረዳ። በአፋር ክልል የዞን ሁለት ዋና ከተማ በሆነችዉ አብአላ ዉስጥ የሚኖሬት ቁጥራቸዉ 15 ሺ የሚጠጋ የትግራይ ተወላጆች ብዛት ስላለን እራሳችንን የማስተዳደር መብት ይሰጠን ሲሉ ያቀረቡትን ጥያቄ የክልሉ ሰብአዊ መብቶች ሃለፊ የሆኑት አቶ ገአስ አህመድ አዎንታዊ መልስ የማያስፈልገዉና አግባብ የሌለዉ ተራ ጥያቄ ነዉ ሲሉ የትግራይ ተወላጆች ያቀረቡትን ጥያቄ አጣጥዉታል።

አቶ ጋአስ በዱብቲ ከተማ በርካታ የአማራ፣ የኦሮሞ እና የትግራይ ተወላጆች ቢኖርም አንድም ቀን የወረዳ ጥያቄ አለማንሳታቸውን ገልጸው፣ ከመቀሌ በ45 ኪሎሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው አብአላም ከተማ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ያቀረቡት ጥያቄ አሳዛኝ መሆኑን ገልጸዋል። የአፋር ክልል በህወሀት ሰዎች የሚመራ መሆኑን የገለጹት አቶ ገአስ፣ ተወላጆቹ ወረዳ ይሰጠን ከሚሉ ክልሉ የራሳቸው መሆኑን ቢያውቁት ይሻል ነበር ብለዋል። እንደ አቶ ገአስ አባባል አብላ ከተማ ዉስጥ የሚኖሩት የትግራይ ተወላጆች ከተማዋ በራሳቸዉ ቋንቋ ሽከት ተብላ እንድትጠራና እንዲሁም የአፋር ክልላዊ መንግስት በከተማዋ መሬት ለኢንቨስትመንት መስጠት አይችልም የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳታቸዉን ጠቅሰዉ በአሁኑ ጊዜ በአፋር ክልል የህወሀት ባለስልጣናት ግምገማ እያስደረጉና የራሳቸውን ሰዎች እየሾሙ ክልሉን ለውድመትና ለጥፋት እየዳጉት መሆናቸዉን ተናግረዋል።

## የወያኔ ፖሊሶች ከግንቦት7 ህዝባዊ ኃይል ጋር ግንኙነት አለዉ የሚሉትን ወጣት ሁሉ እየከበቡ ማሰር ጀመሩ

የዘረኛዉ ወያኔ የፖሊስና የጸጥታ ኃይሎች በቅርቡ እራሱን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋራ ካስተዋወቀዉ ከግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ጋር ግንኙነት አለዉ ብለዉ የሚጠረጥሩትን ወጣት እያደኑ ማሰር መጀመራቸዉን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ታማኝ የአገር ዉስጥ ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ በዘገበዉ ዜና ገለጸ። ለኢሳት የደረሰው መረጃ መሠረት መሳሪያ አንግበዉ ከአዲስ አበባ በብዛት የተንቀሳቀሱ የፌደራል ፖሊስ አባላት ከባህርዳር በ35 ኪሜ ርቀት ላይ ወደምትገኘዉ መርአዊ የምትባል ከተማ በመሄድ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን አፍነው አዲስ አበባ ዉስጥ ለግዜዉ ወዳልታወቀ ቦታ እንደወሰዷቸዉ ለማወቅ ተችሏል።

ምሽት ላይ አድፍጠዉ መርአዊ ከተማ የገቡት ፖሊሶችና የደህንነት ኃይሎች የአካባቢውን ሰዎች በማስፈራራት ተማሪዎቹን አፍነው የወሰዱዋቸው ሲሆን፣ በወቅቱ አንድ ወጣት ክፉኛ መደብደቡን ለማረጋጥ ተችሏል። አንድ የባህር ዳር ነዋሪ ለግንቦት ሰባት ዜና ዜና ዝግጅት ክፍል ስልክ ደዉለዉ የተማሪዎቹን መታሰርና መደብደብ ካወገዙ በኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ አንቅሮ እንደተፋዉና ስርአቱን ለመደምሰስ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝ የተረዳዉ ወያኔ የቀብፀ ተስፋ እርምጃ መዉሰዱ የሚገርም ባይሆንም አይኑ ያተፈበትንና ገደብ የሌለዉ እጁ የደረሰበትን ዜጋ ሁሉ እያፈሰ ማሰር መጀመሩ ህዝብ የጀመረዉን የፍትህ፤ የነጻነትና የደሞክራሲ ትግል አጠናክሮ የድሉን ግዜ ያፋጥነዋል እንጂ አያሳጥረዉም ብለዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ የደህንነት ሹም በመሆን ለረጅም ጊዜ ያገለገለዉ የሻለቃ መሳፍንት ጥጋቡ ወያኔን በመክዳት የግንቦት7 ህዝባዊ ሀይልን መቀላቀሉ ታውቋል። ሻለቃ መሳፍንት በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ስላለው የዘር ችግር፣ በብአዴን ውስጥ ስለሚነሱ ቅሬታዎች እና መሰል ጉዳዮች ዛሬ ከኢሳት ጋር ሰፊ ቃለምልልስ አድርጓል። ሙሉ ቃለምልልሱ በቅርቡ ይቀርባል።

## የጠ/ሚኒስትር ሀይለማርያም ፓርላማ ዉሎ የፓርላማዉን አባላት ጭምር ማስቆጣቱ ታወቀ

የወያኔ ታማኝ ሎሌ የሆነዉ ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ባለፈዉ ሳምንት የፓርላማ ዉሎዉ 40 በ 60 የተባለውን የቤቶች ልማት ፕሮጀክት አስመልክቶ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠዉ ምላሽ ከዚህ ቀደም ባልተለመደ መልኩ ከዚህ ቀደም ማስቆጣቱ ተሰማ፡፡ ኃይለማርያም ደሳለኝ ይህ እንግዳ የሆነ ተቃዉሞ የገጠመዉ የ2005 በጀት ዓመት የስምንት ወራት ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት ሲሆን የፓርላማዉ አባላት 40 በ 60 የሚባለው የቤት ልማት መቶ በመቶ የመክፈል አቅም ላላቸው ሰዎች ቅድሚያ ይሰጣል የመባሉን ጉዳይ እርግጠኛ ስለመሆኑ ለጠየቀዉ ጥያቄ አዎንታዊ መልስ በመስጠቱ ወይም መቶ በመቶ የመክፈል አቅም ላላቸው ቅድሚያ እንደሚሰጥ በማረጋገጡ ፓርላማዉ በተቃዉሞ ድምፅ ሲሞላ ተስተዉሏል።

ለወያኔ ፓርላማ ቅርበት ያላቸው ምንጮች የፓርላማዉ አባላት ለምን አለወትሯቸዉ ጠ/ሚኒስትር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ላይ እንዳልጎመጎሙ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ቀደም ሲል ፕሮግራሙን በተመለከተ ለፓርላማው በቀረበዉ ሪፖርት 40 በ60 የሚባለው ፕሮግራም መካከለኛ ገቢ ያለውን በተለይም በደሞዝ የሚተዳደረውን የህብረተሰብ ክፍል ይጠቅማል ተብሎ መነገሩንና ሆኖም በዕቅድ ደረጃ ለባለአንድ ክፍል መኝታ ቤት 857 ብር፣ለባለሁለት መኝታ ቤት 1 ሺ 337 ብር፣ ለባለሶስት ምኝታ ቤት ደግሞ 2 ሺ133 ብር ለአምስት ተከታታይ ዓመታት በየወሩ መቆጠብ እንዳለበት መታቀዱ የመካከኛ ገቢ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል አቅም ያገናዘበ አይደለም የሚል ቅሬታ በፓርላመዉ አባላት ዘንድ በቅሬታ መልክ በተደጋጋሚ ይነሳ እንደነበረ አስታውሰዋል፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ መካከለኛ ገቢ አለው የሚባለው በተለይም የመንግስት ሰራተኞች አማካይ ወርሃዊ መካከለኛ ገቢ ከ2 ሺ 500 ብር እንደማይበልጥ ምንጫችን ጠቅሶ ከዚህ ደመወዝ ላይ ዝቅተኛውን በወር 857 ብር መቆጠብ እንዴት ይቻላል ሲል የወያኔን ግራ የሚያጋባ አሰራር ገና ሳይጀመር ጥያቄ ዉስጥ የገባ አሰራር ነዉ ብሎታል፡፡ በዚህ ምክንያት የ40 በ60 የቤት ልማት ፕሮግራም መካከለኛ ገቢ ላላቸዉ ሰዎች ይዘጋጅ እንጂ እካሁን ድረስ እየጠቀመ ያለዉ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ነዉ፤ ይህንን ደግሞ ኃ/ማሪያም ደሳለኝም ፓርላማ ዉስጥ ባደረገዉ ንግግር አረገግጦታል ብሏል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጠ/ሚኒስተር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ ቢሮ አማካይነት በተደረገው ጥናት ለውጪ ኩባንያዎች ዝግየሆነውን የሸቀጦች ችርቻሮ ንግድ ስራ ለመፍቀድ ወይ ሌሎች አማራጮችን ለማየት መሞከሩን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አዋሽ ወንዝ የሚሊዮኖችን ህይወት በእጁ እንደያዘ አደጋ ላይ መዉደቁ ተሳማ

የብሉምበርግ ዜና ወኪል ሰራተኞችና አክስፐርቶች አዋሽ ወንዝና አካባቢዉን አጥንቶ ባወጣዉ ዜና መሰረት ወንዙንና አካባበዊን በተመለከተ እጅግ በጣም አስደንጋጭ ዜና ለአለምና ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሰማቱ ከሰሞኑ ተሰማ። በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኘው የበሰቃ ሀይቅ በመስኖ ስራዎች እና በተፈጥሮ እንቅስቃሴ ምክንያት ጨዋማነቱ በ15 እጥፍ በመጨመሩና በየአመቱ በክረምቱ ወራት ዝናብ በዘነበ ቁጥር ሀይቁ ወደ አዋሽ ወንዝ መፍሰስ ስለሚጀምር ይህ አደገኛ አዝማሚያ ከአሁኑ ፈጣኝ እርምጃ ካልተወሰደ ወንዙን ለመጨረሻ ጊዜ ከጥቅም ውጭ ያደርገዋል የሚል ከፍተኛ ፍራቻ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በ1960ዎቹ 3 ስኬር ኪሎ ሜትር ብቻ የነበረዉ የበሰቃ ሐይቅ ዛሬ ከ45 ስኬር ኪሎሜትር በላይ መድረሱ በኤክስፐርቶቹ ተጠንቶ የተደረሰበት ሲሆን ሀይቁ ከልማት ስራ ጋር በተያያዘ በተፈጠረ የአፈር መሸርሸርና በመሬት የውስጥ እንቅስቃሴ ምክንያት ጨዋማነቱ ከመጠን በላይ እየጨመረ በመሄዱ የሚሊዮኖችን ህይወት ለአደጋ አጋልጧል።

የወያኔ የውሀና ኤነርጂ ሚኒስቴር የከርሰ ምድር ውሀዎች ዋና ሀላፊ የሆነዉ አቶ ተስፋ ታደሰ በግልጽ እንደተናገረዉ “ሀይቁ በራሱ ጊዜ ወደ አዋሽ መፍሰስ ከጀመረ የአዋሽ ወንዝ ለዘላለሙ ከጥቅም ውጭ ይሆናል” ብሏል። በሌላ በኩል ደግሞ የላይኛው አዋሽ ወንዝ የውሀ ጥናት ባለሙያ የሆነዉ አቶ እንደሻው ታደሰ ደግሞ የሰኔ ዝናብ ከመዝነቡ በፊት ሀይቁ ወደ አዋሽ ወንዝ እንዳይፈስ ወሳኝ ጥረት መደረግ አለበት ሲሉ አሳስበዋል። ባለሙያው እንደሚሉት ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ የሚገኘው ሀይቅ ወደ ወንዙ ከፈሰሰ ከተሞችን ከማጥለቅለቅ አልፎ የአካባቢውን አርብቶ አደሮች ሊያፈናቅላቸው ይችላል።

ብሉምበርግ ሰፋ ባለዉ ጥናታዊ ዘገባዉ እንገለጸዉ የወያኔ አገዛዝ ላለፉት 14 አመታት የውሀ ፓምፖችን በመጠቀምና በዮችን በመስራት በሰቃን ለመቆጣጠር ጥረት ቢያደርግም አልተሰካላትም። በአለማያ ዩኒቨርስቲ የሲቪል የኢንጂነርግ ዲፓርትመንት አስተማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር መገርሳ ዲንቃ እንደተናገሩት በአካባቢው የሚደረገው የመስኖ ስራ ችግሩን አባብሶታል። ፕሮፌሰሩ የመሬት እንቅስቃሴው ለሀይቁ መስፋፋት ተጨማሪ አስተዋጽኦ አድርጎ ሊሆን እንደሚችልም ገልጸዋል። ሀኖም ስህተታቸዉንና ጥፋታቸዉን በተቃዋሚዎች ላይ ወይም ባለፉት መንግስታት ላይ ብቻ ማላከክ የሚቀናቸዉ የወያኔ ባለስልጣናት ከዚህ ቀደም በላይኛው አዋሽ ላይ ሲካሄድ የነበረው የመስኖ እንቅስቃሴ ችግሩን እንዳባባሰው ለማመን ባይፈልጉም በሁኔታዎች ተገድደዉ የችግሩን ስፋትና ጥልቀት አለማመን ተገደዋል።

## ነጻነትን ከነጻ አውጭዎች የምንጠብቅበት ጊዜ ላይ አይደለንም!

ነጻነት እኛ ሰዎች በልደት ወደዚህ አለም ስንመጣ አብሮን የሚመጣ የተፈጥሮ ፀጋ ነዉ። ነጻነት ከሌሎች የምንጠብቀዉ ወይም ማንንም ስጠን ብለን የማንጠይቀዉ ፈጣሪ ለእያንዳንዳችን ያደለንን፤ በዚህ አለም ቆይታችን ለደቂቃም ቢሆን እንዲለየን መፍቀድ የሌለብን ኃብት ነዉ። ነጻነታችን እጃችን ላይ ሲኖር በግለሰብ ደረጃ የምንደሰትበት፤ እንዳንቀማ በጋራ የምንጠብቀዉና እንደወያኔ አይነቱ ፀረ ህዝብ ኃይል ሲቀማን ደግሞ በጋራ ታግለን ማስመለስ የሚገባን የግልና የጋራ ኃብት ነዉ። ዛሬ ከ21 የወያኔ አመታት በኋላ እኛ ኢትዮጵያዉያን በድህነትና በረሀብ የምንጠቃዉ፤ በዘረኝነት አለንጋ የምንገረፈዉ፤ የምንሰደደዉ፤ የምንታሰረዉና የምንገደለዉ ይህንን ፈጣሪ ያደለንን ነጻነት የሚባል ኃብት ወያኔ አንድ፤ ሁለትና ሦስት እያለ ሲቀማን አፋችንን ዘግተንና እጃችንን አጥፈን ስለተመለከትን ነዉ። መፈናቀላችን፤ ስደታችን፤ ዉርደታችንና በገዛ አገራችን ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ መኖራችን እንዲያበቃ ለማድረግ ያለን ብቸኛ አማራጭ ሌሎች መጥተዉ ነጻ ያወጡናል ከሚለዉ አመለካከት ተላቅቀን ነጻነታችንን ለማስመለስ ህዝባዊ ትግሉን መቀላቀል ብቻ ነዉ።

ነጻነታችንን የቀሙን የወያኔ ዘረኞች ነጻነታችንን እንደቀሙን ለረጂም አመታት ለመግዛት እንዲመቻቸዉ በዘር፤ በቋንቋ፤ በክልልና በሐይማኖት ከፋፍለዉን ከሃያ አንድ በፊት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ጀመሩትን እስራት፤ ስደት፤ ግድያና ዝርፍያ አሁንም እንደቀጠሉ ነዉ። የወያኔ ዘረኞች ነጻነታችንን ቀምተዉ እየገዙን ቢሆንም ገዛናቸዉ ብለዉ እጃቸዉን አጣጥፈዉ አልተቀመጡም። ዜጎች ነጻነታቸዉንና መብታቸዉን እንዳይጠይቁ አፋቸዉን ያዘጋሉ፤ አንዱ ለሌላዉ አንዳይቆም አገር፤ ባንዲራና ኢትዮጵያዊነት የሚባሉ ትላልቁቹን የጋራ እሴቶቻችንን በየቀኑ ያፈርሳሉ። ይህ የሚያሳየን ዜጎች ትልቅ ተስፋ ይዘዉ፤ ቤተሰብ መስርተዉ ለራሳቸዉና ለአገራቸዉ የሚኖሩበት ግዜ እየጠፋ ተስፋ መቁረጥ፤ ስደትና የመከራ ኑሮ ዘመን እየከበበን መምጣቱን ነዉ። ይህ ከሆነ የነገዋን የነጻነት፣ የፍትህ፣ የዴሞክራሲ ባለጸጋ ኢትዮጵያን ለማየት እያንዳንዱ ዜጋ በቻለው አቅሙ ሁሉ ጠንክሮ በመታገል እና ከራሱ ባለፈ ሌላው ዜጋ የነጻነት ትግሉን ጎራ እንዲቀላቀል ብሎም የዚህ ትግል ባለቤት እንዲሆን እንጠይቃለን፡፡ የሀገራችን ህዝብ የነጻነት ችቦ አቀጣጣይ የትግሉ አካል በመሆን መስራት እንጅ፣ ከቶ ሌላ አካል፣ ሌላ ሃይል መጦ ነጻ ያወጣኛል በሚል በባርነት እየተገዛ መጠበቅ የለበትም። ነጻነትና ዴሞክራሲ በችሮታ አሊያም ከሰማይ እንደሚወርድ መና የሚጠበቅ ስጦታ አይደለም። ነጻነት የራስን መሰዋእትነት ይጠይቃል። አለበለዚያ "ላም አለኝ በሰማይ ወተትዋንም አላይ" እንዳይሆን ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ የዘር በትር አለንጋ የሚደርስበት ግርፋት፣ ስቃይ፣ ርሃብ፣ ስደት፣ እንግልት በራሱ በህዝቡ ላይ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ራሱ ለራሱ ነጻነት፣ በእምቢ አልገዛም ባይነት የሚነሳበት ጊዜው አሁን ነው። ነጻነትን ከነጻ አውጭዎች በመጠበቅ እስከመቼ የወያኔ የጥይት ሰለባዎች እንሆናለን?

ወገን ሁሉ ለራሱ ነጻነት፣ ህልውና ሲል የለውጡ እንቅስቃሴ ታጋይ የመሆን ኢትዮጵያዊ ግዴታውን እንዲፈጽም ጥሪ እናደርጋለን፡፡ ለአገሩ፣ ለማንነቱ መሰዋእትነት ለመሆን እንደሚኮራ ሁሉ አገሩም በሱ ትኮራለች፡፡

በርግጥ ነው በህወሃት/ኢህአዴግ የአሰቃቂ ዘመናት ስለአገራችን የፖለቲካ ጉዳይ ማሰብና መናገር ወንጀልና ሽብርተኛ አስደርጎ በጠራራ ፀሐይ የሚታሰሩበትና በግፍ የሚገደሉበት ጊዜ ነው። ይህንን አድርገሃል ተብሎ ሳይሆን ይህንን ሳታስብ አትቀርም ተብሎ ያለምንም ህጋዊና በቂ ምክንያት ወጣቶች፣ አረጋውያን ያለጊዜያቸው፣ ያለዕድሜያቸው በከንቱ አልቀዋል። በቅርቡም ደግሞ በአማራው ተናጋሪ የተጀመረው ዘርን የማጥፋት ዘመቻ አንዱ ነው። ስለዚህ እስከ መቼ ነው ለራሳችን ነጻነት ሌላ አካል ነጻ እስኪያወጣን የምንጠብቀው? ከዚህ በላይ ምን ስቃይ አለ? ሀገር የጠፋች እለት ምን ሊውጠን ይችላል።

እማማ ኢትዮጵያ ለልጆቿ ህልውናዋን ከመፍረስ አደጋ እንዲጠብቋት፣ ከወያኔ የዘርና ዘረኝነት አደጋ እንዲታደጓት ስትማጸን፤ ልጆቿ ደግሞ አንዳች ሃይል መጥቶ ነጻነታቸውን ያጎናጽፋቸው ዘንድ የኢትዮጵያ አምላክ እያሉ ሲጠባበቁ እስከ መቼ? ስለዚህ ወጣት ጎልማሳ አዛውንት ሽማግሌ ዘር ጾታ ሳይለይ የዛሬ የነጻነትህ ትግል ጅማሮ እጅህ ላይ ነው። ሀገራችን የዛሬውን የወያኔን ጨለማ ሸኝታ የነገውን የነጻነት ብርሃን እየጠበቀች ብቻ ሳይሆን እየናፈቀች አለች። ያንን ድቅድቅ ጨለማ ሰንጥቆ የሚወጣ የወጣት ጀግኖች ልጆቿን ብርኃን ትናፍቃለች። እናም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የብርሃኑ መታያ ችቦ ሆኖ ታሪክ ይሰራ ዘንድ ለነጻነቱ የሚታገልበትና ትግሉን የሚቀላቀልበት ሰአት እየፈጠነ፣ እየቆጠረ፣ እየቀረበ ነውና ተነስ ባለህበት ያለህን አንሳና ወርውር፣ አቀብል።

ቋንቋችን አንድ ነው ለነጻነትህ ታገል! በማንነትህ በብሄር ምክንያት በተወለድክበት ሀገር፣ ቀዬ አትሰደድ! በሀገርህ ምድር እንደ ሁለተኛ ዜጋ የመኖሪያ ፈቃድ ጠያቂ አትሁን! ወንድምህ፣ እህትህ፣ አባትህ እናትህ ባልሰሩት ወንጀል ወደ እስር ቤት ሲታጎሩ፣ ሲገደሉ ዝም ብለህ አትይ! በሀገርህ ስብእና ክብርህ ተዋርዶ አትመልከት! ተነስና መብራቱን አብራ! ጀግኖች መከታ ሊሆኑህ ከጎንህ ተሰልፈዋል።

በአሁኑ ወቅት አያሌ ኢትዮጵያዉያን ወያኔን ለመታገል መሳሪያ ካነሱ ከነጻነት ታጋዮች ጋር በየቀኑ እየተቀላቀሉ ቢሆንም፤ ሀገር ውስጥ ያላችሁ እለታዊ ኑሮን ለማሸነፍ ስትሉ በየፋብሪካው በመንግስት ሴክተሩ እና ሌሎች ተቋማት የምትገኙ ሁሉ በድጋሜ ግንቦት 7 እንደሁሌው ሁሉ የውስጥ አርበኛ ሆናችሁ የነጻነት ትግሉን መቀላቀል፣ ራሳችሁንና ሀገራችሁ ከወያኔ የዘረኛ ማዳፍ እጅ ነጻ ትወጣ ዘንድ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳትሉ ትግሉን ቀጥሉበት። ፍርሃታችሁን በጥሳችሁ በመደራጀትና መረጃ በማስተላለፍ ግዴታችሁን ተወጡ። ለሀገራችሁ ቅርብ ሁኑ! ለነጻነት ትግሉ፤ የትግል ስልትና የተለየ የትግል ቦታ ሳትመርጡ ወያኔን ያስወግዳል በምትሉት ስልትና ይመቸናል በሚሉት ቦታ ሁሉ እስከመጨረሻው ትታገሉ ዘንድ አደራችን ነው።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና ዴሞክራሲ ንቅናቄ ዛሬም ቢሆን የህዝባችን ሰበአዊ መብትና ነጻነትን ገፈው ሕግን ያፈረሱ ህገ አራዊት የሆኑትን ወያኔዎች ከሀገራችን ምድር ላንዴና ለመጨረሻ ግዜ በማስወገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በእኩልነትና በነጻነት የሚኖርባትን ሀገር ለመመስረት የሚያደርገውን የትግል ጉዞ ይቀጥላል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## በደል እንዴት ይረሳል!!. . . (ከገጽ 4 የዞረ)

ይረሳል አኝዋክ በተኛበት በወያኔ እባብ ሲነደፍ። በደል አንዴት ይረሳል የእርሻ መሬት በሰዉ ገላ ሲደለደል . . . . በደል እንዴት ይለመዳል አኝዋክ በቁሙ ሲገደል መሬቱን ተቀምቶ ስጋዉ በአሩር ሲነደል።

እስኪ አስበዉ ወገኔ በደል እንዴት ይረሳል ቤተሰብ ለእልቂት ሲሰለፍ፤ እንዴት ይለመዳል በደል ባል ሚስቱ ፊት ታስሮ ሲገረፍ አባት እናትና ልጅ ለመታረድ ሲሰለፍ። እባክህ ንገረኝ በደል እንዴት ይረሳል አኝዋክ እንደበሬ ሲጠለፍ አጅና እግሩን ታስሮ ሲገረፍ . . . . . እንዴት ይለመዳል በደል ክቡር የሰዉ ገላ እንደቅጠል ሲረግፍ።

አረ ምነዉ . . . .ምነዉ አልደፈፍር አለ ልባችን አልቆርጥ አለ ሀሞታችን . . . . . እኮ ምነዉ አልሰነዝር አለ እጃችን፤ ወያኔ ዘር ለይቶ ሲፈጀን ሽብርተኛ እያለ ሲፈርጀን ተራ በተራ እየለቀመ ሊፈጀን። ምነዉ . . . አረ ምነዉ . . . . . ምንድነን እኛ በሬ ነን ወይስ ጌኛ ሲረግጡን ሲገድሉን ዝም ብለን የምንተኛ። ማነሽ አንቺ . . . ማነህ አንተ አበሻ ነህ ወይስ ፈላሻ ቱለማ ነህ ሜጫ ገፍተዉ ሲጥሉህ የማትንጫጫ እምትወቀጥ እንደሙቀጫ። እስኪ ንገረኛ ማነህ አንተ? አደሬ ነህ ተጉለቴ ጎጃሜ ነህ ይፋቴ እባክህ ነገረኝ በሞቴ። በልኮ ንገረኝ ጉራጌ ነህ ሲዳማ፤ ሃዲያ ነህ ሱማሌ ምንድነህ ንገረኝ ኦሮሞ ነህ ወይስ አማራ እንዳባቶችህ የማታቅራራ።

ምንም ሁን ምን ሁሉም መልካም ነዉ . . . ማንነትህ ግን አንድ ነዉ . . . . ኢትዮጵያዊነት ነዉ ....አዎ! ማንነት ኢትዮጵያዊነት ነዉ

ኢትዮጵአዊነት ደግሞ ድፍረት ነዉ
አትንኩኝ ባይነት ጀግንነት ነዉ
ኢትዮጵያዊነት . . . .አኝዋክ ሲገደል አላስገድል ማለት ነዉ . . .
አማራ ሲፈናቀል ፈንቃዩን መፈንቀል ነዉ

አዎ! ኢትዮጵያዊነት እንደ እስክንድር ጽናት ነዉ . . .
እንደ አንዱ አለም እምቢ ማለት ነዉ
ኢትዮጵያዊነት እንደ መይሳዉ ለአገር መሞት ነዉ ....
እንደ ዬኔሰዉ መስዋዕት መሆን ነዉ . .

እንደ ዬኔሰዉ . . . . . . እንደ ዬኔሰዉ . . . . . እንደ ዬኔሰዉ
መስዋዕት መሆን ነዉ!

---

## የጠ/ሚኒስትር ሀይለማርያም ፓርላማ ዉሎ የፓርላማዉን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የኢሳት ቴሌቭዥንና ሬድዮ ዘጋቢ ጠቅሶ ይህ ነገር ግን ትልልቆቹ ኩባንያዎች በሸቀጦች የችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ ቢደረግ የአገር ውስጥ አስመጪዎች በአጭር ጊዜያት ውስጥ ከገበያ ውጪ በማድረግ መንግስት ሊቆጣጠረው የማይችለው ገበያ ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት በመኖሩ በመንግስት ቁጥጥር ስር ሆኖ ዋጋ የማረጋጋትና አነስተኛ ዋጋ ካላቸው ገበያዎች ሸቀጦችን በመግዛት በተመጣጣኝ ዋጋ የሚያቀርብ ኢንተርፕራይዝ እንዲቋቋም ውሳኔ ላይ ተደርሶአል፡፡

# የ"አብዮታዊ ዲሚክራሲ" መንገድ የት ያደርሳል ?

አብርሃም ደስታ

ወቅቱ የአካባቢና ከተሞች "ምርጫ" የሚካሄድበት ነው ። ሰለ "ምርጫ" ሲታሰብ ስለ አማራጮች ማሰላሰል ግድ ነው። አንድ ፖለቲካዊ ምርጫ ምርጫ የሚያሰኙት ነገሮች ምንድን ናቸው? ምርጫው ዲሞክራሲያዊና የተሟላ እንዲሆን አማራጮች (ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች) መኖር አለባቸው። ምክንያቱም በምርጫ የሚመርጥ ህዝብና የሚመረጡ የፖለቲካ ድርጅት ተወካዮች መኖር አለባቸው። መራጩ ህዝብ በአግባቡ መምረጥ እንዲችል ለምርጫ ሰለሚቀርቡ ፓርቲዎች በቂ መረጃ ሊኖረው ይገባል።

ህዝቡ በቂ መረጃ እንዲኖረው በምርጫ የሚቀርቡ ፓርቲዎች በነፃነት ተንቀሳቅሰው ከህዝቡ ተገናኝተው አማራጭ ፖሊሲዎቻቸውና ዓላማቸው ማስተዋወቅ ይኖርባቸዋል። እነዚህ ፖሊሲዎችና ዓላማዎች ለማስተዋወቅ ነፃና ገለልተኛ የግል ሚድያዎች መኖር አለባቸው። መራጩ ህዝብም በነፃነት የፈለገውን የመምረጥ መብት ሊከበርለት ይገባል።

ስለዚ በምርጫ የፖለቲካ ድርጅቶች ማቅረብ የሚጠበቅባቸው "የሚመረጡ ሰዎች" ብቻ ሳይሆን ለመመረጥ የሚያስችላቸው የፖሊሲ አቅጣጫዎች ጭምር ነው ። የኢትዮድያ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢህአዴግ ዓፋኝ ስለመሆኑ ይነግሩናል። ኢህአዴግም በበኩሉ ተቃዋሚዎች አማራጭ ፖሊሲዎች እንደሌላቸው ያስረዳል። ነገር ግን ተቃዋሚዎች አማራጭ ፖሊሲ ይኑራቸው አይኑራቸው "አለን" የሚሉትን ነገር ለህዝብ እንዲያቀርቡት ተፈቅዶላቸዋል ወይ? ፖሊሲ እንዳላቸው ወይ እንደሌላቸው መወሰን ያለበት መራጩ ህዝብ አይደለምን ? የተቀዋሚዎች አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫ ለማወቅ እንቸገር ይሆናል። ምክንያቱም ገዢው ፓርቲ በሚፈጥረው የመረጃ ዓፈና (የግል ሚድያ ዓፈና)፣ የፖለቲካ ሙስና፣ የኢኮኖሚ ሽበራ፣ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ወዘተ የተቀዋሚ ፓርቲ ተወካዮች ከህዝቡ ጋር ተገኛኝተው መግባባት ተስኗቸዋል። በአንፃሩ ደግሞ ገዢው ፓርቲ ኢህአደግ የመንግስትን ሃብት (ለምሳሌ የኢትዮድያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት) ለግል ፕሮፓጋንዳ በማዋል፣ግለሰዎችን በጥቅማጥቅሞች በመደላል፣ ከምርጫ ደምብ ውጪ የራሱ ሚድያ በመጠቀም (ለምሳሌ ህወሓት ድምፂ ወያነ ሲኖረው ኢህአዴግ ደግሞ ሬድዮ ፋና አለው) ከህዝብ ጋር ያለ ገደብ የመገናኘት ዕድል አለው። ኢህአዴግ ታድያ ከህዝብ ጋር እየተገናኘ የትኛው አማራጭ ይዞ ነው የሚቀርበው? ተቀዋሚዎች አማራጭ ፖሊሲ ከሌላቸው ኢህዴግስ ይኖረው ይሆን?

ስለ ኢህአዴግ አማራጭ አቅጣጫ ስናስብ ስለ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ማስታወሳችን አይቀርም። "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" የገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ አፌስየላዊ አይዲዮሎጂ (ርእዮተ ዓለም) ተደርጎ ይወሰዳል። የአብዮታዊ ዲሞክራሲ መንገድ የት ያደርሳል? አብዮታዊ ዲሞክራሲ መንገድ አለው? ወይስ ራሱ መንገድ ነው? "አብዮታዊ ዲሞክራሲ አይደዮሎጇ (ርእዮተ ዓለም) ነው" ካልን "አይዲዮሎጂ" ምንድ ነው? አይዲዮሎጂ የአንድ የፖለቲካ ድርጅት (ወይ ድርጅቶች) የሚከተለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ የሚከተለው የፖለቲካ ኢኮኖሚ አቅጣጫ ነው። አቅጣጫው አመክኖያዊ ቀጣይነትና ተከታታይነት(Consistency of interrelated ideas) ባላቸው ሐሳቦች ተዘጋጅቶ ለሁሉም ዘርፎች መንገድ የሚያሳይ ነው። የአንድ አይዲያሎጂ ዓላማ ልማት ማምጣት ነው። ልማት የሚመዘገብባቸው መንገዶች ግን ሊያዩ ይችላሉ። ልማት ለማምጣት የሚሳተፉ ተዋናዮች ሁለት ናቸው። መንግስትና ገበያ (State vs market) አይዲዮሎጂዎች የሚመጡ ታድያ "ልማት ለማምጣት የየትኛው ሚና (የመንግስት ወይ የገበያ) ከፍ (ወይ ዝቅ) ማለት አለበት?" ከሚል እስቤ የሚመነጩ ናቸው። ስለዚ ልማት (ግብ)ና አይድያሎጂ (መንገድ) እስቤያቸው ፓለቲካ ኢኮኖሚ መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ መሰረት "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" እንደ "አይዲዩሎጂ" ወስደን እንገምግመው። የአብዮታዊ ዲሚክራሲ መነሻ ምንድ ነው? ማሌሊት (ማርክሲስት ሊኒኒስት ሊግ ትግራይ) ነው። ህወሓት ተዋጊ ቡድን በነበረበት ግዜ ዝንባሌው ወደ ከሚኒስት ሀገራት ያደላ ነበር። ከሚኒስታዊ አስተሳሰብ በሀገራችን (እንዲሁም በአሁና ዓለማችን) እንደማይሰራ አያውቁም ነበር። ምክንያቱም " ኮሚኒስት ሀገር ወይ ፓርቲ ሊኖር አይችልም።

There cannot be a "communist state or party", because if we reach the stage of communism, there will not be state. In a communist stage, there is no private property. If there is no private property. there is no politics. If there is no politics, there is no state If there is no state, there isno political party. Therefore, the very assumption of communist state or party is wrong. Yet, the essence of "Communist state or party" is state Capitalism.

ህወሐት ማሌሊት ሲመሰርት የግንዛቤ ችግር ነበረው ብዮ አሰባለሁኝ ። ህወሐት ስለ ርእዮተ ዓለም ሙሉ ግንዛቤ ባይኖረውም ማሌሊትን የመስረተበት ምክንያት ግን ሳይኖረው አይቀርም። ተዋጊ ቡድን እንደመሆኑ መጠን ግራ ዘመም አቅጣጫ መያዙ ግድ ይላል፣ ተራማጅ ሃይል ለመመሰረት ። በዛን ግዜ " ማርከሲስቶች ነን "የሚሉ State Capitalists ተራማጆች (progressive) ሲባሉ የምዕራባውያን individual capitalists ደግሞ አድሃርያን (reactionaries) በሚል ተሰይመው ነበር። ስለዚ progressive ለመሆን "ማርክሲስቶች" መሆን ሳይመርጡ አልቀረም። ህወሓቶች ያንን የጫካ አስተሳሰብ እንደማይሰራ በከፊል የተገነዘቡ ስልጣን ከያዙ በኃላ ነው። አሁን ሁለቱም (የማርክሲስትና የካፒታሊዝም) ፅንስ ሓሳቦች ቀላቅለው (ከግዜው ጋር አብሮ ለመጓዝ) አይዲዮሎጂያቸው "አብዮታዊ ዲሞክራሲ" መሆኑ ነገሩን። የ"አብዮታዊ ዲሞክራሲ" ፅንስ ሃሳብ ምንድ ነው? የአይድዮሎጅው social base (የሚደግፈው ወይ እንዲደግፈው የሚጠበቅ የሕብረተሰብ ክፍል) የትኛው ነው? አንድ አይድዮሎጂ መሰፍርቱ (1) social base መታወቅ አለበት፤ (2) ድጋፍ እንዲሰጥ የሚጠበቅ የሕ/ሰብ ክፍል በአመክንዮ የተደገፈ መሆን አለበት። (3) አይድዮሎጂውን የሚያራምድ ፓርቲ ድጋፍ የሚሰበሰበው (ወይ በምርጫ የሚያሸንፈው) ህዝብን በሓሳብ በማስመን (ከአይዲዮጂው የመነጩ ሓሳቦች) መሆን አለበት ። በነዚህ መስፈርቶች ታድያ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ Social base ማነው? ነጋዴው? ከተሜው? ሰራተኛው? ባለሃብቱ?... በትክክል አይታወቅም። በአንድ ወቅት ግን መለስ ዜናዊ "የአብዮታዊ ዲሞክራሲ Social base ገበሬው ነው" ሲለን አስታውሳለሁ ። እንደ መለስ አገላለፅ "አብዮታዊ ዲሞክራስዊ ገበሬው ማእከል ያደረገ ነው? ፅንስ ሓሳቡን በደምብ ተነግሮናል? ኢህአዴግ በምርጫ ለማሸነፍ የሚጠቀመው ስትራተጂ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሓሳቦች (ideals) ለህዝብ በማስረዳት ነው? ወይስ በጭቆና? ኢህአዴግ በስልጣን ያለው " አብዮታዊ ዲሞክራሲ " በተሰኝ "አይዲዮሎጂው" ትክክለኛነት ለህዝብ አሳምኖ፣ ህዝቡም በምክንያታዊነት ደግፎት አይደለም። (በመጀመርያ) የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ሓሳብ ምን እንደሆን በትክክል አይታወቅም (ሁለተኛ) ኢህአዴግ ስልጣን የያዘው (በስልጣን ያለው) በህዝብ ድጋፍ ሳይሆን በሃይሉ (በጠመንጃ) ነው። (ሦስተኛ) የፓርቲው መሰረት ቤተሰባዊነት ነው፣ ሙስና ነው፣ እህል ውኃ ነው ፤አይዲዮሎጂው አይደለም። ስለዚ "አብዮታዊ ዲሚክራሲ" እንዳ አማራጭ አይደዮሎጂ ሊወስድ አይችልም። አንድ የፖለቲካ ድርጅት ስልጣን ከያዘ (አይዲዮሎጂ ቢኖረውም ባይኖረውም) አንዳንድ ተግባራት ማከናወኑ አይቀርም። "ኢህአዴግ እያከናወናቸው ያሉ ተግባራት ከአብዮታዊ ዲሚክራሲ የመነጩ ናችው" ካልን እስቲ የተወሰኑ እንይ። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እሳቤ የቡደን መብት ከግል መብት ይቀድማል ። ቅድሚያ የሚሰጣቸው የኢትዩድያ ብሄር ብሄረሰዎችና ህዝቦች ናቸው። እነኚህ ብሄር ብሄረሰዎችና ህዝቦች ግን ሰዎች ናቸው። ማንኛውም ብሄርና ብሄረሰብ ግለሰዎች አሉት።

የሁሉም ህዝቦች ወይ ቡዱኖች መሰረት ግለሰብ ነው። "ብሄርና ብሄረሰዎች" የግለሰዎች ስብስብ ስሞች ናቸው። የግለሰብ ሁለንታናዊ መብት ከተከበረ የብሄርና ብሄረሰዎች መብትም መከበሩ አይቀርም። ኢህአዴግ ግን የግለሰዎች መብት እያጣሰ የብሄረብሄረሰዎች መብት አከብራለሁ ይላል። ስለዚ "አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስሕተት ነው።

በ"ቡድን መብት" መሰረት የኢትዮድያ ብሄር ብሄረሰዎችና ህዝቦች "የየራሳቸውን ሃብት" (በየክልላቸው) own ያደርጋሉ። እንዲውጤቱም የአንድ ክልል ተወላጆች በሌላ ክልል (በገዛ ሀገራቸው) መኖር የመቻላቸው ተስፋ እየጨለመ ነው። አማርኛ ተናጋሪ ኢትዮድውያን ከደቡብና ቬኑሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የተፈናቀሉበት (ከቀያቸው የተባረሩበት) መንገድ ከዚህ "ቡድን መብት" ከሚል የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና የመነጫ ነው። የ"ቡድን መብት" አስተሳሳብ የ"ከፋፈለህ ግዛ ፓሊሲ" በመተግባር ኢትዮድያውን እርስበርሳቸው አንድነት እንዳይኖራቸውና ገዥውን መደብ በአንድነት እንዳይቃወሙ፣ ጥቅማቸውና ደህንነታቸው እንዳያስከብሩ ለማሰናከል የታለመ ነው። ይህን አስተሳሰብ ታድያ የኢትዮድያ ሀገራችን አንድነት የሚፈታተን፣ በህዝቦች አለመተማመንና የጥላቻ ፖለቲካ እንዲሰፍን የሚያደርግ ነው። ስለዚ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ ለኢትዮድያ የሚጠቅም አይደለም ። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ፍልስፍና መሰረት መሬት የመንግስት ነው። መሬት መሸጥ ወይ መለወጥ አይፈቀድም። መሬት እንዳይሸጥ ወይ እንዳይለወጥ የተደረገበት ምክንያት መሬት እየተሸጠ በተወሰኑ ባለሃብቶች እጅ ተካማችቶ ሌላው ድሃ ገበሬ መሬት አልባ እንዳይሆን ታስቦ ነው። ይሄንን ሓሳብ ግን ምክንያታዊ አይደለም። (አንደኛ) "መሬት ይሸጥ ይለወጥ" ስለተባለ ብቻ " ገበሬው መሬቱ ያለአግባብ ይሸጣል "ብለን መደምደም አንችልም። ገበሬው (ይሁን ሌላ የሕብረተሰብ ክፍል) የሚያዋጣውና የማያዋጣው በደምብ ያውቃል። ምናልባት ይሄንን ሓሳብ ከተጠራጠርን ግን መንግስት ለህዝቡ አስፈላጊው (የመሬት ገበያ በተመለከተ) መረጃና ስልጠና መስጠት ይችላል። የገበሬው በሬ (ሊሸጥ ወይ ሊለወጥ) ስለሚችል ብቻ ሁሉም (ወይ አብዛኞች ) በሬዎች ተሸጠው በተወሰኑ ባለሃብቶች ሲሰበሰቡ አላየንም።

(ሁለተኛ) አንድ ገበሬ መሬት ለመሸጥ ወይ ለመለወጥ የሚገደደው አስቸጋሪ ሁኔታ ሲገጥመው እንጂ መሸጥ ስለሚችል ብቻ አይደለም። ለምሳሌ አንድ ገበሬ ሊታመም ይችላል። መታከምያ ገንዘብ የለዉም። የራሱ መሬት ካለው (መሸጥ ከቻለ) ግን ሽጦ ታክሞ ድኖ ሰርቶ መሬቱን እንደገና ገዝቶ ማስመለስ ይችላል። መሬት የመንግስት ከሆነ (መሸጥ ካልቻለ) ግን ለሕክምና የሚሆን ገንዘብ ስለማይኖረው ህይወቱ ሊያጣ ይችላል። (ሦስተኛ ) ገና ለገና ገበሬዎች መሬታቸው ሊሸጡ ይችላሉ ተብሎ መንግስት ቀምቶ ይውሰደው ? መንግስት እኮ ህዝብን የማገልገል ግዴታ እንጂ የህዝብ ሃብት (ለምሳሌ መሬት) የመውሰድ መብት የለውም። "መሬት እንዳይሸጥ" በሚል ሰበብ ዜጎችን መሬት በግል እንዳይዙ ማድረግ ተገቢ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የ“አብዮታዊ ዲሚክራሲ” መንገድ

. . . (ከገጽ 3 የዞረ)

አይደለም። (አራተኛ) መሬት የመንግስት እንደሆን ከተወሰነ መንግስትና ገዢው ፓርቲ በተቀላቀሉበት ሀገር መሬት የገዢው ፓርቲ ከድሬዎች መሆኑ አይቀርም። በዚህ ምክንያት ካድሬዎች በፈለጉት ግዜ ገበሬዎችን እያፈናቀሉ መሬታቸው እየነጠቁ ለፈለጉት ሰው (ባለሃብት) ሊሰጡት ይችላሉ። የዜጎችን መፈናቀል ይከተላል። በሌላ በኩል ደግሞ ለም መሬታችን ለውጭ ዜጎች በርካሽ ዋጋ ይሸነሸናል። ከኢትዮድያውን ይልቅ ለውጭ ዜጎች ቅድሚያ እየተሰጠ ይገኛል። (አምስተኛ) መሬት የመንግስት በመሆኑ ዜጎች መሬት ከመንግስት ተከራይተው (በሊዝና በፖለቲካ ታማኝነት) ሲጠቀሙ መንግስት ኪራይ እየሰበሰበ በስልጣኑ ተደላድሎ ይኖራል። እንደውጤቱም መንግስት ኪራይ ሰብሳቢ ሁነዋል። “አብዮታዊ ዲሞክራሲ” የዲሞክራሲ መርሆች አሉት? ስልጣን ለህዝብ ይሰጣል ? ገዢው ፓርቲ የያዘው ስልጣን ከህዝቡ ተውሶ የተረከበው ነው ወይስ በራሱ የዘረፈው ነው? አብዮታዊ ዲሞክራሲ “የሕግ የበላይነት ይቀበላል ? በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሁሉም ነገር ከሕግ በታች ነው ። ሁሉም ነገር ሕግ በሚፈቅደው መሰረት ይከናወናል። የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ፍርድ ቤት ነፃና ገለልተኛ እንዲሆን ዳኞች (ናሌሎች) ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ፣ የማያዳሉና በሙያው (በህግ) እውቀት ያላቸው መሆን ይጠበቅባቸዋል። አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለዚህ ዓይነት ሁኔታ ይፈቅዳል ? ወይስ ፀረ ዲሞክራሲ ነው ? በዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሕግ የበላይነት ለማስከበር ሕጉን መተርጎም ያለበት ፍርድ ቤት ነው (በአንዳንድ ሀገሮች ሌላ ዓይነት አሰራር ሊኖር ይችላል። ዞሮ ዞሮ ሕግ ተርጓሚዎች ግን ገለልተኛ፣ የሕግ እውቀት ያለቸው ናቸው)። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እሳቤ ግን ሕግን የመተርጎም ስልጣን የተሰጠው ለፌደሬሽን ምክር ቤት ነው ። የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላት ግን ፖለቲከኞች ናቸው ፣ በገዢው ፓርቲ የተመረጡ የፓርቲው አባላት ናቸው ። ሕግን የመተርጎም ስልጣን ከተሰጣቸው ታድያ ፓለቲካ ከሕግ በላይ ሆነ ማለት ነው። ፓለቲከኞች (የሕግ ሂደትን በማጣስ ) በፈለጉት መልክ ፓለቲካዊ ትርጓሚ (ውሳኔ) እንዲሰጡ ያስችላቸዋል። በዚ መሰረት ፓለቲከኖች ከሕግ በላይ ናቸው።

ስለዚህ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ የሕግ የበላይነት የለም። የዜጎች ዋስትና ደግሞ ሕገ መንግስት ነው። ስለዚ አብዮታዊ የለም ። የዜጎች ዋስትና ደግሞ ሕግ መንግስት ነው። ስለዚ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ችግር አለበት። ኢህአዴግ የግብርና መር ኢንድስትሪ (ADLI) ፖሊሲ እንዳለው ይነግረናል። ይህንን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለ 21 ዓመታት የተፈለገውን ለውጥ ሳያመጣ ቆይተዋል። ኢህአዴግ ህዝብን ለማታላል “ጥሩ ፖሊሲ አለው። ችግሩ ያለው አፈፃፀም ላይ ነው” ይለናል። ግን አንድ ፖሊሲ ጥሩ ሆኖ እንዴት የአፈፃፀም ችግር ይኖረዋል? የአፈፃፀም ችግር ያለበት ፖሊሲ እንዴት ጥሩ ፖሊሲ ሊባል ይችላል? አንድ ፖሊሲ ከሕልም የሚለይበት ዋናው ቁምነገር አፈፃፀሙ ነው ። ፓሊሲ ካልተፈፀመ ፓሊሲ ሊባል አይችልም፣ ምክንያቱም የማይፈፀም ከሆነ ሕልም ነው ። አንድ ፖሊሲ ወጥቶ የአፈፃፀም ችግር ካጋጠመው ፖሊሲው እንደገና መፈተሽ አለበት።

ፓሊሲ ወደ ግብ የሚወስድ መንገድ ነው። ግቡ ልማት ማምጣት ነው። ፓሊሲው በአሰፋልት መንገድ እንመሰለው። “አስፋልት መንገዱ ጥሩ ነው” የምንለው በተጠበቀው መሰረት አሽከርካሪዎችን ማስተናገድ ሲችል ብቻ ነው። (ሲፈፀም) አገልግሎት መስጠት ካልቻለ (ተሽከርካሪዎችን ማሳለፍ ካልቻለ) ጥሩ መንገድ ነው ልንል አንችልም። ፖሊስም እንደዛው ነው ።ፓሊሲ ወደ ግብ የሚወስድ መንገድ ነው። ግቡ ልማት ማምጣት ነው። ፓሊሲው በአሰፋልት መንገድ እንመሰለው። “አስፋልት መንገዱ ጥሩ ነው” የምንለው በተጠበቀው መሰረት አሽከርካሪዎችን ማስተናገድ ሲችል ብቻ ነው። (ሲፈፀም) አገልግሎት መስጠት ካልቻለ (ተሽከርካሪዎችን ማሳለፍ ካልቻለ) ጥሩ መንገድ ነው ልንል አንችልም። ፖሊስም እንደዛው ነው። የአፈፃፀም ችግር ካለው ፖሊሲው ስህተት ነው ማለት ነው ። ምክንያቱም ፖሊሲ የሚወጣው እንዲፈፀም ተደርጎ መሆን አለበት። “አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስህተት ነው” ካልን ታድያ የኢህአዴግ አማራጭ ፓሊሲ (የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት የሚጠቀመው ሓሳብ ወይ መንገድ) ምንድነው ? ዓፈና ነው። ኢህአዴግ በስልጣን ላይ ያለው ዓፈና እንደ መሳርያ አይዲዮሎጂ በመጠቀሙ ነው። ስለዚ የኢህአዴግ አይዲዮሎጂ አብዮታዊ ዲሞከራሲ ነው ካልን አብዮታዊ ዲሞከራሲ ገዥው ፓርቲ በስልጣን ለመቆየት የሚጠቀመው የዓፈና ስትራተጂ ነው ብንል እንሳሳትም። የገዦው ፓርቲ ዓላማ በሰልጣን መቆየት ነው። በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ስም በሁሉም ዘርፎች ጣልቃ የመግባት ስትራተጂ ይከተላል። ለምሳሌ ገዢው ፓርቲ በኢኮኖሚው ዘርፍ ጣልቃ ሲገባ እንደሌሎች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲዎች ኢኮኖሚውን ለማነቃቃት ሳይሆን ለመቆጣጠር ነው። ዋነኛ የሚባሉ የኢኮኖሚ ሴክተሮች በቁጥጥሩ ስር ናቸው:: በትምህርት ቤቶች፣ በሃይማኖቶች፣ በተለያዩ የሲቪክ ማሕበራት ጣልቃ ይገባል::

ሰለዚህ ኢህአዴግ ሰላማዊ የሓሳብ አማራጭ የለውም ። አማራጩ ሃይል መጠቀም ነው ። ሰሞኑ እየተካሄደ ባለው ምርጫ ያቀረበው አማራጭም ያው በሃይል የተደገፈ ዓፈናው ነው። ዜጎችና የተቃዋሚ ፓርቲዎች በማፈን ብቻውን እየተወዳደረ ነው። ብቻውን ሮጠ ብቻውን አሸናፊ ለመኖን። ተወዳዳሪዎች በሌለበት “ምርጭ”ም ቢሆን ኢህአዴግ የራሱ ጥላ ማመን አልቻለም። ምክንያቱም በሃይል ድጋፍ የሚኖር ሁሉ መሰረቱ በቀላሉ ሊናጋ የሚችል ነው። ግን የአሁኑ ምርጫ ምርጫ ሊባል ነው ? ምርጫ ‘ምርጫ’ የሚሆነው ኣማራጮች ሲኖሩት ነው። የኣሁኑ ምርጫ ኣማራጮች ኣሉት? መራጩ ህዝብ ስለነዚህ ኣማራጮች ሙሉ መረጃ ኣለው? መረጃው የተገኘው ከነፃና ገለልተኛ ሚድያ ነው? ለመሆኑ ነፃ ሚድያ ተፈቅዷል? ህዝቡ መረጃ የማግኘት ሙሉ መብት ኣለው? ህዝቡ የሰጠው ድምፅ እንደሚከበርለት ዋስትና ኣለው?

## በደል እንዴት ይረሳል!!

. . . ( ክፍል 2 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ)

አቶ አጋላና ወ/ሮ አቻላ ብዙም ሳይሄዱ ሁለት ልጆቻቸዉን አኙኮ ከዋጠ የጨለማ ሀይል ጋር ፊት ለፊት ተፋጠጡ። አኝዋክን ከገዛ መሬቱና ከገዛ ቤቱ እየጎተተ ሲገድል ያመሸዉ የወያኔ ገዳይ ቡድን እንደገና የሚገድለዉ ሲያገኝ በድን እንዳገኘ ጥምብ አንሳ ተደሰተ። . . . . . . . . .ከመሸ ዬት ነዉ የምትሄዱት አላቸዉ አለ ያ አፋም ጠመንጃዉም መቅደም የሚቀናዉ የወያኔ ገዳይ ቡድን መሪ፤ . . . . . ልጆቻችንን ፍለጋ ነዉ የምንሄደዉ . . . .ለመዝሙር ልምምድ እንደሄዱ አልተመለሱም አሉ ወ/ሮ አቻላ ረጋ ባለና በሰከነ ድምጽ። ወ/ሮ አቻላ መሳሪያ የታጠቀ የወገን ሀይል አገርን ከጠላት ሲያድን ነዉ እንጂ የገዛ ወገኑን ሲገድል አይተዉም ሰምተዉም ስለማያዉቁ ፊት ለፊታቸዉ የቆመዉና የሁለት ልጆቻቸዉን ህይወት የቀማዉ ነፍሰ ገዳይ ቡድን እነሱንም እንደማይምር አልገባቸዉም። ቢያዉቁማ ኖሮ እሳቸዉም እንደልጃቸዉ እንደ አማኑኤል ወግድ ብለዉት ቢገድላቸዉም በጅግንነት ይሞቱ ነበር።

ለወያኔ መሪዎችና ለአግአዚ ነብሰ ገዳዮች እዉነት፤ርህራሄና ፍቅር ነዉ እንደ ክምር ድንጋይ የከበዳቸዉ እንጂ ሰዉን ማሰቃየትና መግደልማ የተካኑበት ስራቸዉ ስለሆነ ምንም አይሰማቸዉም። የወያኔዎች ሰዉ ካልገደሉ አገር የመሩ አይመስላቸዉም፤ የአግአዚ ገዳዮች ደግሞ ሂዱና ግደሉ ሲባሉ “ስንት እንግደል” ነዉ እንጂ ለምን እንግደል ብሎ የሚጠይቅ አዕምሮ የአብሯቸዉ ስላልተፈጠረ መግደልን አንደ ሙያ የያዙ የጫካ ዉስጥ አዉሬዎች ናቸዉ። እንግዲህ ከዚያ ፍቅር ካሞቀዉ ጎጆ ልጆቻቸዉን ፍለጋ የወጡት አባትና እናት ከእንደነዚህ አይነቱ መንታ የጥፋት ሀይል ነዉ ጋር ነዉ በዉድቅት ሌሊት ፊት ለፊት የተፋጠጡት። አዎ! የዋሆቹ አቶ አጋላና ወ/ሮ አቻላ ሁለት ልጆቻቸዉን በጭካኔ የገደለዉን አረመኔ የወያኔ ሀይል ነበር ልጆቻችንን አፋልጉን ብለዉ የሚደራደሩት።

“ኑ” ተከተሉኝ . . . . . ልጆቻችሁ ወዳሉበት ቦታ ልዉሰዳችሁ አለ . . . . ያ ልክ እንደ ፖሊስ ዉሻ የሱን ቋንቋ የማይናገርና እሱን የማይመስል ሁሉ ጠላት የሚመስለዉ የአግአዚ ወታደር። አቶ አጋላና ወይዘሮ አቻላ እዉነትም ልጆቻቸዉን የሚያዩ መሰላቸዉና ያ” ቀኑን ሙሉ እንደ ከሰል ከስሎ የዋለዉ ፊታቸዉ በፈገግታ ተሞላ። የአኝዋክ ህዝብ ቃሉን አክባሪ እንግዳ አሳዳሪ ህዝብ ነዉ። በአኝዋክ ባህል ከአፍ የወጣ ቃል መከፈል ያለበት ዕዳ ነዉ። አኝዋኮች ቀልድና ጨዋታ ይወዳሉ ግን ቀልድን ከቁም ነገር አይደባልቁም። በአኝዋክ ወግና ደንብ አንድ ሰዉ አዋቂ ነዉ ተብሎ የሚከበረዉ እዉነትና ዉሸት መደባለቅ ሲተዉ ብቻ ነዉ። ለዚህ ነዉ የዋሆቹ ወ/ሮ አቻላና አቶ አጋላ “ልጆቻችሁን ላሳያችሁ” የሚላቸዉ የወያኔ ባንዳ ሰዉ መስሏቸዉ ኑ ልጆቻችሁ ጋ እንሂድ ሲላቸዉ ደስ ብሏቸዉ የተከተሉት። የሚቀጥለዉን የግማሽ ሰአት ያክል “የመስቀል ጉዞ” ባልና ሚስት ዬት ነዉ ቦታዉ ወይም መቼ ነዉ የምንደርሰዉ ብለዉ ሳይጠይቁ የአግአዚ ገዳዮችም አንዲት ቃል ሳይተነፍሱ አግአዚ ጠመንጃዉን ባልና ሚስት ነጠላቸዉን እንደያዙ በዝምታ መንገዱን ተያያዙት።

ሀምራዊ ቀለም እንደተቀባ ድፎ ዳቦ ሰማዩን የሞለችዉ ሙሉ ጨረቃ ምሽቱን ቀን አስመስላዋለች፤ አልፎ አልፎ የሚነፍስ አየር ድምጽ ቢሰማም ጫካዉና ቁጥቋጦዉ እንደ ሰዉ የተኙ ይመስል ፖቻላ ዉስጥ ሁሉም ነገር ዘጭ . . . እረጭ ብሏል። አልፎ አልፎ የሚሰማ ድምጽ ቢኖር ከጀበርናዉ ጋር የእየተጋጨ የሚያቃጭለዉ የወያኔ ገዳዮች ጠመንጃ ድምጽና እንደ ገና በግ ወደ መታረጃ ቦታቸዉ የሚሄዱት ባልና ሚስት ዱካ ብቻ ነዉ።

ወ/ሮ አቻላ እግራቸዉን መሰንዘር እስኪሳናቸዉ ድረስ ሰዉነታቸዉ ዝሏል፡ ሆኖም ከአሁን አሁን ልጆቼን አያለሁ የሚል ተስፋ ጉልበት ሆኗቸዉ ባለቤታቸዉን በግማሽ እርምጃ ቀድመዉ የማያዉቁትን የማታ ጉዞ ታያይዘዉታል። እኩለ ሌሊት ሊሆን ትንሽ ሲቀረዉ መንታ መንገድ ላይ ደረሱ። በቀኛቸዉ ወንዝ በግራ በኩል ደግሞ ተከርክሞ የተሰራ የሚመስል ኮረብታ ጉብ ጉብ ብሏል። ከወንዙ ባሻገር በሩቁ አነስተኛ መንደር ይታያል። ባልና ሚስትን ለመግል አመቺ ቦታ ሲፈልጉ ያመሹት የወያኔ ነፍሰ ገዳዮች ይጠብቁት የነበረዉ ግዜ ደረሰ። ወንዙን ለመሻገር ሁለት እርምጃ ሲቀራቸዉ አቶ አጋላ በፍጥነት የሚጓዝ መኪና እንደገጨዉ ሰዉ ከባለቤታቸዉ ኋላ መሬቱ ላይ በፊት ለፊታቸዉ ወድቀዉ ተከሰከሱ . . . . . . . . እኔን ይድፋኝ ብለዉ ወ/ሮ አቻላ ባለቤታቸዉን ለማንሳት ጎንበስ ሲሉ ያ የሴት ልጃቸዉን የማጂንን ሰዉነት ሁለት ቦታ የከፈለዉ የአግአዚ ሳንጃ የሳቸዉንም አናት ለሁለት ከፈለዉ።“እኔን ይድፋኝ” በዚህ ምድር ላይ የወ/ሮ አቻላ የመጨረሻዉ ድምጽ ነበር። የቤቴል ቤ/ክርስቲያን መዘምራን ቡድንን፤ፓስተር ኡጁሉን፤ ማጂንን፤ አማኑኤልንና እናቱን በአንድ ምሽት የጨፈጨፈዉ የወያኔ ነፍሰ ገዳይ ቡድን አቶ አጋላን የወደቁበት ቦታ ከጨረሳቸዉ በኋላ ሌላ የሚገደል አኝዋክ ፍለጋ ከወንዙ ማዶ ወዳለቸዉ መንደር አቀና። እንደ ብዙዎቹ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ባህል በአኝዋክም ባህል ልጅ አባቱን እንጂ ወላጅ ልጆቹን አይቀብርም ይባላል። እድሜ ለወያኔ ዘረኞች . . . እነ አማኑኤል ግን እነሱ ወላጆቻቸዉን ወላጆቻቸዉም እነሱን መቅበር አልቻሉም ።

አንግዲህ . . . . የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ እንዴት ይረሳል እንዲህ አይነት በደል . . . . .በላ ንገረኝ እንዴት ይለመዳል የዘር ማጥፋት ወንጀል ። . . . . እባክህ ንገረኝ በደል እንዴት ይለመዳል የሰዉ ስጋ እንደ ክትፎ ሲከተፍ በደል እንዴት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ**
**እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org